# ቅዱሳን መላእክት

ከብርሃኑ ጎበና

ቅዱስ ማለት የተለየ፣ የተከበረ፣ የተመሰገነ፣ የተመረጠ ማለት ነው፡፡ ቅዱሳን መላእክት ስንልም የተመሰገኑ፣ ከርኩሳን መላእክት የተለዩ፣ ክቡራን መላእክት ማለታችን ነው፡፡ መላእክት ሁለት ወገን ናቸው፡፡ ብርሃናውያን መላእክትና የጨለማ አበጋዝ የሆነው የዲያብሎስ ሠራዊት የሆኑት እኩያን መላእክት፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መላእክት ከሌሎቹ መላእክት በአጠራር የምንለያቸው ቅዱስ በሚል ቅጽል ነው፡፡ መላእክት መቼ ቀን ተፈጠሩ? መላእክት የተፈጠሩት በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ ነው፡፡ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ /ሃክላኢሜሮን/ ተብሎ በሚጠራው መጽሐፍ እግዚአብሔር መላእክትን በዕለተ እሑድ ፈጥሮ በሦስቱ ሰማያት በኢዮር፣ በራማና በኤረር፤ በከተማ አሥር፣ በነገድ መቶ አድርጎ አሰፈራቸው ብሏል፡፡ አሰፋፈራቸው፡- ኢዮር፡- በኢዮር ያሉትን መላእክት በ4 አለቃ አርባ ነገድ ከፈላቸው፡፡ ኢዮርን እንደ ፎቅ ቤት አድርጎ በአራት ከተማ ከፈላት፡፡

በኢዮር በላይኛው ከተማም አሥሩን ነገድ ስማቸውን አጋእዝት ብሎ በመሰየም አለቃቸው ይሆን ዘንድ ሳጥናኤልን ሾመው (10$1)፡፡ በኢዮር በሁለተኛው ከተማ አሥሩን ነገድ ስማቸውን ሱራፌል ብሎ በመሰየም ሱራፌል የተባለውንም መልአክ አለቃቸው አደረገው (ኢሳ.6$2)፡፡ በኢዮር በአራተኛው ከተማ አሥሩን ነገድ ስማቸውን ኃይላት (ጴጥ.3$22) በማለት ቅዱስ ሚካኤልን በአለቅነት ሾመላቸው፡፡ ራማ፡- ራማ በተባለው የብርሃን ሰማይ ላይ ያሉትን መላእክት ሦስት ከተማ አድርጎ ከፍሏታል፡፡ በመጀመሪያ በራማ የሠፈሩት አሥሩ ነገድ ስማቸው አርባብ ይባላል፡፡ አለቃቸውም ቅዱስ ገብርኤል ነው፡፡ በሁለተኛው ከተማ ያሠፈራቸው አሥሩ ነገድ መናብርት ሲባሉ አለቃቸውም ሩፋኤል ነው። በሦስተኛው ከተማ ያሠፈራቸው አሥሩን ነገድ ስማቸውን ሥልጣናት (1ጴጥ.3$22) በማለት አለቃቸው ይሆን ዘንድ ሱርኤል የተባለውን መልአክ ሾሞታል፡፡ ኤረር፡- ኤረር የተባለውን ሰማይ እንደ ራማ በሦስት ከተማ የከፈለው ሲሆን የቀሩትን ሰላሣ ነገድ በእነዚህ ከተማዎች አሥፍሯቸዋል፡፡መጀመሪያው ከተማ አሥሩን ነገድ መኳንንት (መዝ.3/2$47-10) በማለት ሰደክያል የተባለውን መልአክ አለቃ አድርጎላቸው አሥፍሯቸዋል፡፡
በሁለተኛው ከተማ አሥሩን ነገድ ሊቃናት በማለት አለቃቸው ይሆን ዘንድ ሰላታኤል የተባለውን መልአክ ሾሞታል፡፡ በሦስተኛ ከተማ አሥሩን ነገድ መላእክት (1ጴጥ.3$12) ብሎ ሰይሟቸዋል፡፡ አናንያል የተባለውን መልአክም አለቃቸው አድርጎታል፡፡ በእነዚህ በሦስቱ የመላእክት ሰማያት ላይ የሠፈሩት መላእክት በነገድ መቶ ሲሆን በከተማ ደግሞ አሥር ነበሩ፡፡ ከእነርሱም ሰማልያል /ሳጥናኤል/ አንዱን ነገር ይዞ ከክብሩ ወርዷል (ኢሳ.14$12)፡፡ የመላእክት መላእክት በአፈጣጠራቸው ረቂቃን መናፍስት በመሆናቸው እንደ ሥጋ ለባሽ ፍጥረታት አይበሉም፣ አይጠጡም፣ አያገቡም (ማቴ 22$30፡፡ ሉቃ 24$39)፡፡ ጾታም የላቸውም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ግን መላእክት በአንድ ወቅት ከሰው ልጆች ጋር እንደወደቁ አድርገው ይናገራሉ፡፡ ለዚህም መረጃ አድርገው ለማቅረብ የሚሞክሩት «የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች አገቡ» የሚለውን ኃይለ ቃል ነው (ዘፍ.6$2)፡፡ በዚህ ቦታ ላይ የእግዚአብሔር ልጆች /መላእክት/ ተብለው የተጠሩት ረቂቃኑ መላእክት ሳይሆኑ ሥጋ ለባሽ የሆኑ ደቂቀ ሴት (በአቤል ፈንታ አዳም የወለደው የሴት ልጆች) ሲሆኑ (ዘፍ. 4$25) የሰው ልጆች የተባሉት ደግሞ የቃየል ልጆች ናቸው፡፡ ይኸንንም ምስጢር «አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ሄኖክ» እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡ የሰው ልጆች ከበዙ በኋላ እንዲህ ሆነ፡፡ በዚያ ወራትም መልከ መልካሞች ደመግቡዎች ልጆች ተወለዱላቸው፡፡ በደብር ቅዱስ ያሉ ደቂቀ ሴትም እነሱን አይተው ወደዱአቸው፡፡ እርስ በርሳቸውም ኑ ለኛ ከቃየል ልጆች ሴቶችን እንምረጥ ለኛ ልጆችን እንውሰድ አሉ$ (መጽ.ሄኖክ 1$1-3)፡፡ ደቂቀ ሴት ስለምን የእግዚአብሔር ልጆች /መላእክት/ ተባሉ? 1ኛ. ስለአለቅነታቸው፡- የግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ መላእክት በማለት ይጠራቸዋል፡፡

መልአክ የሚለው ቃል የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አለቃ ማለት ነው፡፡ ቅዱስ መጽሐፍ ‹መልአክ› የሚለውን ቃል «አለቃ» ማለት መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡ ለምሳሌ በዮሐንስ ራእይ 21፣8-12 ላይ ያለውን ቃል ብንመለከት ጥሩ አስረጅ ይሆናል፡፡ በእነዚህ ሥፍራዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ  ተብሎ እናገኛለን፡፡ ይህ መልእክት ደግሞ ለሰማያውያን መላእክት ለነ ቅዱስ ሚካኤልና ቅዱስ ገብርኤል የተላከ እንዳልሆነ የታወቀ ነው፡፡ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች የተላከ እንጂ፡፡ ዛሬ ‹እገሌ የዚህ ደብር አለቃ ነው› ተብሎ እንደሚጠራው ሁሉ #በኤፌሶን ላለች ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ (አለቃ)» ለሚልከው መልእክት «በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ$ ተብሏል፡፡ ደቂቀ ሴትም /የሴቶች ልጆችም/ መላእክት መባላቸው አለቆች በመሆናቸው ነው፡፡ 2ኛ. ስለ ን ጽሕናቸውና ቅድስናቸው፡- ከሴት ልጆች መካከል በደብር ቅዱስ ከሴት ርቀው፣ ንጽሕ ጠብቀው፣ በጾም ተጠምደው፣ የሚኖሩ ስለነበሩ በዚህ ግብራቸው መላእክትን መስለዋልና የእግዚአብሔር ልጆች በመባል ተጠርተዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዝ የሚኖሩትን ሰዎች የእግዚአብሔር ልጆች ይላቸዋል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በቀዳማዊ ክታቡ #የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ$ ብሏል (1ዮሐ. 3$1)፡፡ በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጆች እንደምንሆን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተም�ል፡፡ ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል$ ሲል፡፡ ይህም ደግሞ በጥምቀት የሚገኝ ጸጋ ነው (ዮሐ. 3$1)፡፡

ከላይ በተገለጸው ምክንያት ደቂቀ ሴትን የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ በመጥራት በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር መንገድ ከወጡት ከቃየል ልጆች ጋር በፈጸሙት ዝሙት እግዚአብሔር እንዳዘነባቸው ቅዱስ መጽሐፍ አስረድቷል፡፡ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት ሰማያውያን መላእክት ናቸው የሚለው አመለካከት ስሕተት መሆኑን የምንረዳው ከቅዱስ መጽሐፍ ባገኘነው ትምህርት መሠረት ነው፡፡ ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው የእግዚአብሔር ቃል ሰማያውያን መላእክት በተፈጥ�ቸው /በባሕርያቸው / ማግባት፣ መጋባት፣ መብላት፣ መጠጣት የለባቸውም፡፡ ፍትወተ ሥጋ የሥጋ ለባሹ የሰው ልጅ ተፈጥ�ዊ ባሕርይ ነው፡፡ ስለዚህ ሰማያውያን መላእክት ከሰው ልጆች ጋር በፍትወት አልወደቁም (ማቴ.22$30)፡፡ የመላእክት አገልግሎት ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔርና

በሰው መካከል ለአገልግሎት የሚፋጠኑ ናቸው፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትንና ቸርነትን ወደ ሰው ልጆች፣ የሰዎችንም ጸሎትና ልመና ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ ናቸው፡፡ ስለ ተራዳኢነታቸው - በቅዱሳት መጻሕፍት ቅዱሳን መላእክት በመንገዳችን ሁሉ እንደሚጠብቁን ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል በመንገድ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንነተ ያዝዛቸዋልና፣ እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል$ (መዝ. 90/91/-11)፡፡ ያዕቆብ የልጁ የዮሴፍን ልጆች ምናሴንና ኤፍሬምን ሲባርክ #አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እርሱ እግዚአብሔር፣ ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን የመገበኝ እግዚአብሔር፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ብላቴኖች ይባርክ$ ብሏል (ዘፍ.48$16)፡፡ በዚህም መላእክት ከክፉ ነገር ሁሉ የሚያድኑና የሚጠብቁ እንደሆኑ፣ መባረክም እንደሚችሉ አስገንዝቧል፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት የመላእክትን አዳኝነት ሲያስገነዝብ   የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል፡፡

ብሏል (መዝ33/34/$1)፡፡ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለሕዝበ እግዚአብሔር /ለእሥራኤል/ አገልጋዮቹ መላእክትን ሊያሳዝኑ እንደማይገባ ሲያስጠነቅቃቸው #በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ፣ ወደ አዘጋጀሁትም ሥፍራ ያገባህ ዘንድ፣ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ፤ በፊቱ ተጠንቀቁ፡፡ ቃሉንም አድምጡ፡፡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት$ (ዘጸ.23$20) ብሏል፡፡ የቅዱሳን መላእክት ረዳትነት አስፈላጊ መሆኑን ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል ሲያመለክት «የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ፡፡ እነሆም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ፡፡ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት» (ዳን.10$13) ብሏል፡፡ በተለይ በፍጻሜ ዘመን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ለክርስቲያኖች በአማላጅነቱና በተራዳኢነቱ እንደሚቆምላቸው #ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል$ ተብሎ በነቢዩ በዳንኤል መጽሐፍ ተገልጧል (ዳን.12$1)፡፡ የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት በሁለት መንገድ ነው፡፡ ማለትም የሰውን ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር የሚያደርሱና የእግዚአብሔርንም ምሕረት ለሰው ልጆች የሚያመጡ ናቸው፡፡ በተለይ የሰዎች መከራ፣ ዕንባና ጸሎት ቅድመ እዚአብሔር የሚያደርሱና ለሰዎች ልጆች እንደሚያማልዱ በትንቢተ ዘካርያስ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፏል፡-

የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ እነዚህን ሰባ ዓመት የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከመቼ ነው; አለ...እግዚአብሔር መልሶ ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው፡፡ ስለዚህም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ እንዲህ አለኝ፡፡ ስበክ፡፡ እንዲህም በል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡፡ ... ወደ ኢየሩሳለም በምሕረት ተምልሻለሁ$ (ዘካ.1$12-17)፡፡ ጌታ በዘመነ ስብከቱ የቅዱሳን መላእክትን አማላጅነት በምሳሌ ሲያስረዳ #አንድ ሰው በታወቀች በወይኑ ቦታ ውስጥ በለስ ነበረችው፡፡ ፍሬ ሊለቅም ወደ እርስዋ ሄደ አላገኘም፡፡ የወይኑን ጠባቂም የዛችን በለስ ፍሬ ልለቅም ስመላለስ እነሆ ሦስት ዓመት ነው፡፡ አላገኘሁም፡፡ እንግዲህስ ምድራችንን እንዳታቦዝን ቁረጣት አለው፡፡ እሱም መልሶ እንዲህ አለው፣ ‹አቤቱ የዘንድሮን እንኳን ተዋት፡፡ ዙሪያዋን አፈር እስካስታቅፋት፣ ፍግም እስካፈስሰባት ድረስ፡፡ ምናልባት ለከርሞ ታፈራ እንደሆነ፣ ያለዚያ ግን እንቆርጣታለን›፡፡$ (ሉቃ. 13$7-9)፡፡ በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር የበለስዋ ባለቤት እግዚአሔር ነው፡፡ በለስ የሰው ልጅ ነው፡፡ የወይኑ ጠባቂም ጠባቂ መልአክ ነው፡፡ ፈጣሪያችን በሥራችን አዝኖ በሚፈርድበት ጊዜ አማላጃችችን መላእክት

አቤቱ ጌታ ሆይ ይህቺን ያሁንዋን ብቻ ታገሥ፣ እኛ ተራድተን መልካም ምግባር የማይሠራ ከሆነ እንደፈቃድህ ይሁን$ በማለት በአማላጅነታቸው ይራዳሉ፡፡ ሙሴ እሥራኤል እግዚአብሔርን አሳዝነው ጽኑ ፍርድ ተፈርዶባቸው ሳለ የፈረደውን ፍርድ በምልጃው እንዲያነሣ እንዳደረገው ሁሉ ማለት ነው (ዘጸ 32$10-14)፡፡ የቅዱሳን ጸሎት የሚያርገው በመላእክት እጅ ነው፡፡ ለዚሁም ማስረጃ የሚሆነን በዮሐንስ ራእይ ላይ ተጽፎ የምናገኘው ነው፡፡ #...የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው፡፡ የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር በመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ፡፡$ (ራእይ 8$3-5)፡፡ ስለዚህ ቅዱሳን መላእክት ጸሎታችንን፣ ልመናችንን እና ዕንባችንን በእግዚአብሔር ፊት ያቀርባሉ፡፡ መልስም ያሰጣሉ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም የመላእክትን ተራዳኢነት ሲያስገነዝብ #ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ፣ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን;$ ብሏል (ዕብ. 1$14)፡፡ ስግደት ለመላእክት መስገድ የሚለው ቃል መዋረድ፣ ማጐንበስ፣ መንበርከክ፣ መደፋት፣ በግንባር መውደቅ፣ ግንባርን ምድር አስነክቶ መሬት ስሞ መመለስ ነው በማለት የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ያትታል፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን ስግደት የአምልኮና የጸጋ ተብሎ ይከፈላል፡፡ የአምልኮ ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ ሲሆን የጸጋ ስግደት ደግሞ እግዚአብሔር ላከበራቸው ቅዱሳን ሰዎችና መላእክት የሚቀርብ ነው፡፡ ለቅዱሳት መላእክት የምናቀርበው ስግደት ከላይ እንደተገለጸው የጸጋ ስግደት ነው፡፡ ጸጋ የሚለው ቃል በቁሙ ሲተረጎም ሀብት፣ መልካም ሥጦታ፣ ዕድል ፈንታ፣ ትምህርት፣ ብዕል፣ ክብር፣ ሞገስ የቸርነት ሥ፣ራ አለዋጋ የሚሰጥና የሚደረግ ማለት ነው፡፡[1] የጸጋ ስግደት ስንል እግዚአብሔር የሰጣቸውን ክብርና ሞገስ አምኖ መንበርከክ ነው፡፡ ይህም ራስን ለእግዚአብሔር ከማስገባት የሚመነጭ ነው፡፡ ሰዶምና ገሞራን በእሳት ለማቃጠል የተላኩት መላእክት ወደ ሎጥ ቤት በገቡ ጊዜ ሎጥ በግምባሩ ተደፍቶ ለመላእክቱ እንደሰገደ ተጽፏል (ዘፍ 19$1)፡፡ ኢያሱ ወልደ ነዌ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል በተገለጠለት ጊዜ በግምባሩ ተደፍቶ ለመልአኩ ሰግዶለታል፡፡ በዚህ ጊዜ ቅዱስ ሚካኤል የተቃውሞ አነጋገር አልተናገረም፡፡ «የቆምክባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ» ከማለት በስተቀር (መጽ ኢያሱ 5$13)፡፡ የእሥራአል ንጉሥ የነበረው ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ከእሥራኤል ሽማግሌዎች ጋር ከመሬት ከፍ ብሎ ሰይፉን ዘርግቶ ለተገለጠላቸው ለእግዚአብሔር መልአክ ሰግደውለታል (ዜና መዋዕል ቀዳ 21$16)፡፡ ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በአባል ወንዝ አጠገብ በተገለጠበት ጊዜ ለመልአኩ ለቅዱስ ገብርኤል ራሱን ዝቅ አድርጐ በግንባሩ ወድቆ ሰግዶለታል፡፡ በዚሁም ላይ የግርማውን አስፈሪነት እና አስደንጋጭነት ጠቅሷል (ዳን 8$15)፡፡ ከላይ የተገለጹት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የሚያስገነዝቡን ለመላእክት ቅዱሳን ሰዎች እንዴት አክብረው እንደሰገዱላቸው ነው፡፡ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሐርን ቃል የተናገሩአቸሁን ዋሃቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሮ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው» (ዕብ 13$7) እንዳለው የቅዱሳን አባቶቻችንና ሕይወት አኗኗር ዛሬ ለእኛ መመሪያ ሊሆነን ይገባል፡፡ እነርሱ አድርገው የተጠቀሙበትን ሁሉ እኛም እናደርገዋለን፡፡ እነርሱ ለቅዱሳን መላእክት ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት በስግደት እንደገለጹ እኛም እግዚአብሔር ላከበራቸው

ቅዱሳን መላእክት ፍቅራችንንና አክብሮታችንን በሥዕላቸው ፊት በመንበርከክ በመስገድ እንገልጻለን፡፡ መላእክት ቢገለጡም ባይገለጡም ሕልውናቸው የተረጋገጠ ነውና ክብራቸው ያው ነው፡፡ ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ሲገለጡ እንጂ ካልተገለጡ ሊሰገድላቸው አይገባም ሊሉ ይችላሉ፡፡ በዓይን ዓይቶ በእጅ ዳብሶ ከማመን ሳያዩ የሚያምኑ ብጹዓን እንደሆኑ ጌታችን አስተምሯል (ዮሐ 20$29)፡፡ ስለዚህ እነዚህ ቅዱሳን አባቶች በዓይናቸው ዓይተው፣ በጆሯቸው ሰምተው ያደረጉትን እና ያመኑትን ለእኛ በማስተላለፋቸው እኛም የእነርሱን ዓይን ዓይን አድርገን ማእነርሱ አይተዋቸው የሰጡትን ክብር እንሰጣቸዋለን፡፡ መገለጣቸውና አለመገለጣቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸውን ክብር አይጨምረውም አይቀንሰውምና ክብራቸው አንድ ነው፡፡ ስለዚህ ይሰገድላቸው ዘንድ የሚገባ ከሆነ ሲገለጡ ሳይገለጡ የሚል ሁኔታ መፈጠር የለበትም፡፡ ለእግዚአብሔር በመንፈስ የአምልኮት ስግደት እንደምንሰግድ ሁሉ (ዮሐ 4$24) እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ አብረው ለሚገኙት ቅዱሳን መላእክትም የጸጋ ስግደት በእምነት ማቅረብ ይገባል፡፡ እነርሱም እግዚአብሐር ባለበት ቦታ ሁሉ አሉና፡፡ ራእ 19$10 («አትስገድልኝ») አንዳንዶች ተጠራጣሪዎች ደግሞ ለመላእክት ሲገለጡም ሆነ ሳይገለጡ ምንም ዓይነት ስግደት አይገባቸውም በማለት ራእ 19$10 («አትስገድልኝ») ላይ ያለውን ይጠቅሳሉ፡፡ በመሠረቱ ይህ ጥቅስ ለመላእክት የጸጋ ስግደት መስግድ እንደሚገባን እንጂ መስገድ እንደማይገባን የሚገልጽ አይደለም፡፡ ወንጌላዊውና ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ለመልአኩ መስገዱ ሳያውቀው ሳይረዳው ያደረገው ድርጊት እንዳልሆነ እንድናምን ማንነቱና ሕይወቱ ያስገነዝበናል፡፡ ምክንያቱም የጥበብ፣ የማስተዋል፣ የዕውቀት ጸጋን የሚያድል መንፈስ ቅዱስ አድሮበት እያለ ሳያውቀው አደረገው ብሎ መናገርና ማመን መንፈስ ቅዱስን እንደ መጽረፍ /መስደብ/ ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ሰው የሚያመልከውንና የሚሠራውን ሁሉ የሚያውቅ ነው፡፡ በተለይ ቅዱስ ዮሐንስ አካል ከሕልውና ተገልጾለት ምሥጢረ መለኮትን የተናገረ ታላቅ ሰው ሆኖ ሳለ ትንሺ ጉዳይ ተሰውራው ለመልአኩ ሳያውቅ ሰግዶ ተግሳጽ ደረሰበት ብሎ ማመን ሞኝነት ብቻ ሳይሆን ክህደትም ጭምር ነው፡፡ የመንፈስ ቅዱስን ሰላም ማቃለል ነው፡፡ #መንፈስ ቅዱስ የሰደበ ደግሞ ኃጢአቱ አይሠረይለትም፡፡$ (ማቴ 12&31-32)፡፡ የመልአኩ አነጋገር ታዲያ እንዴት ይተረጎማል? መልአኩ ቅዱስ ዮሐንስን አትስገድልኝ ማለቱ ስለ ሁለት ነገር ነው፡፡ 1ኛ ስለ ትኅትና ዲያብሎስ ከሥልጣኑ የተሻረው ከክብሩ የተዋረደው በትዕቢቱ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ ቅዱሳን መላእክት ግን ትሕትናን ገንዘብ ያደረጉ በመሆናቸው እንደ ሰይጣን ስገዱልን የሚሉ አይደሉም፡፡ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ይከበሩ ዘንድ ፈቃዱ በመሆኑ የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲወዷቸውና እንዲያከብቧቸው አድርጓል፡፡ ለዮሐንስ በሰገደለት ጊዜ  አትስገድልኝ$ ማለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የሚያወጣ ለጣኦት እንደመስገድ የሚያስቆጥር ሆኖ ሳይሆን መልአኩ ራሱን በዮሐንስ ፊት ዝቅ ከማድረጉ የተነሣ ስለ ትሕትና የተናገረው ነው፡፡ አንድ ሰው ሌላውን ሰው አክብሮ እጅ ቢነሣው /ከመቀመጫው ሲነሳና ሲቀበለው/ ሪ ረ አይገባም እንደሚለው ሁሉ ማለት ነው፡፡ ለዚሁም ማረጋገጫ የሚሆነን (ለትሕትና የተናገረ መሆኑን) በምዕራፍ 19 የሰጠውን ማስጠንቀቂያ በምዕራፍ 21 ላይ መድገሙ ነው፡፡ ለትሕትና የተናገረው መሆኑን ያወቀው ዮሐንስ ለመልአኩ ክብር መስጠት እንዳለበትና መስገድ እንደሚገባው ዐውቆ ድጋሚ ሲገለጥለት በድጋሚ ሰግዶለታል፡፡ 2ኛ ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል የቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ ኮከብ ቅዱስ ጳውሎስ የካህናትን ሥልጣን አስመልክቶ ሲያስተምር #ካህናት ሰውን ሁሉ እንደሚዳኙ አታውቁምን? እናንተ ሰውን ሁሉ የምትዳኙ ከሆናችሁ ይህን ትንሹን ነገር ልትፈርዱ አይገባችሁምን? የዚህንስ ዓለም ዳኝነት ተውትና መላእክትን ስንኳ እንድንገዛ አታውቁምን$ (1ቆሮ 6&2-3) ብሏል፡፡ ከዚህ ትምህርቱ የምገነዘበው ካህናት በሥልጣናቸው መላእክትን ስንኳ ሳይቀር እንደሚያዙ ነው፡፡ ይህንንም ከቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ትምህርት እንረዳለን፡፡ በ344 ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተማ የተወለደው ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እምነትንና ፍቅርን፣ ትዕግሥትንና ትሕትናን፣ በአንድነት ገመድ አስሮ ሕዝቡን ለ7 ዓመት ወንጌልን ሰብኳል፡፡ በ387 ዓ.ም በአንጾኪያ ከተማ ፖትርያርክነት ተሾሞ ሳለ አንድ ጉዳይ ይገጥመዋል፡፡ ንጉሡ አርቃድዮስና ንግሥቲቱ አውዶክያስ ልጅ እየወለዱ እየሞተባቸው አላድግ ስላላቸው የዚህን ምክንያት ቢጠይቁ ደግ ሰው ክርስትና ባያነሣላችሁ ይሆናል ስላሏቸው ከዮሐንስ አፈወርቅ የበለጠ ደግ ሰው በዘመናችን አለን? በማለት ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ መጥተህ ክርስትና አንሣልን ብለው ላኩበት እርሱም ጥሪውን አክብሮ ሲሆድ በመንገድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከተላከ መልአክ ጋር ይገናኛል፡፡ የበቃ ነውና ረቂቁን መልአክ ሊያየው ችሏል፡፡ ዮሐንስም መልአኩን «ወዴት ትሄዳለህ?» ብሎ ጠየቀው መልአኩም ሲመልስለት «አሁን አንተ የምትሄድባትን ብላቴና ነፍሷን ከሥጋዋ ለይተህ አምጣ ብሎኝ የታዘዝኩትን ለመፈጸም ወደዚያ መሄዴ ነው» ይለዋል፡፡ ዮሐንስም «ቆየኝ በጥምቀት ሀብተ ውልድና፣ ስመ ክርስትና ከተሰጣት በኋላ የታዘዝከውን ትፈጽማለህ፡፡ እስከዚያው ግን ከዚሁ አትንቀሳቀስ» ብሎት በሥልጣነ ክህነቱ ገዝቶት ሄደ፡፡ መልአኩም የዮሐንስን ግዝት ጠብቆ ባለበት ቆመ፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ልጅቷን ካጠመቃት በኋላ ንግቶት በሌላ መንገድ ተመለሰ፡፡ የካህናት ሥልጣናቸው የማይናቅ፣ ትእዛዛቸውም ክብር የሚገባው መሆኑን ስለሚያውቅ ያ መልአክ ወደ ላይም ወደታችም ሳይል አሥር ዓመት ከዚያው ሥፍራ ቆሞ ኖረ፡፡ አሥር ዓመት ሲሆናት ለባል ታጨች ያጠመቅካት ብላቴና እነሆ ለአቅመ ሔዋን፣ ባል ልታገባ ነውና መጥተህ ባርከህ ስደዳት ብለው ለዮሐንስ አፈወርቅ ላኩበት፡፡ እርሱም በጥሪው መሠረት ከዛሬ አሥር ዓመት ልጅቱን ሊያጠምቅ ሲሔድ በሄደበት መንገድ መልአኩን ቆሞ አገኘው፡፡ #ምነው ከዚህ ቆመሃል?$ አለው፡፡ መልአኩም ሲመልስለት #የካህናት ማዕረጋቸው የከበረ ነውና መች ወዲያ ወዲህ ያሰኛል፡፡ ቃልህን አክብሬ አንተ ቆይ ካልከኝ ወዲያና ወዲህ ብዬ አላውቅም$ አለው ቅዱስ ዮሐንስም በዝንጉዕነቱ ራሱን ወቅሶ መልአኩን የታዘዘውን ያደርግ ዘንድ አሰናብቶታል፡፡ ከላይ በተገለጸው ታሪክ ብናይ በፍጥሞ ደሴት መልአኩ ለዮሐንስ ወንጌላዊ አትስገድልኝ ማለቱ ዮሐንስ ካህንም ነውና ሥልጣኑ ሊያከብር እንደሚገባው ለመግለጽ ሽቶ ነው፡፡ በክብር ዮሐንስ ከመልአኩ ይበልጣልና፡፡ ---------------------------- ------------------------------------------ /ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 743/